ቅዱስ ሲኖዶስ
The Holy Synod
4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

Date : 04.12.2012.
No. 2070/2012.

# የትንሣኤን በዓል አስመልክቶ የሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ያስተላለፈው ቃለ ቡራኬ

## ተነሥቷል በዚህ የለም

"እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ።" ማቴ 28፥6

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!

በሀገር ውስጥና በዓለም ዙሪያ የምትኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በሙሉ እንኳን የትንሣኤውን ብርሃን ለማየት አበቃችሁ በዓሉም የሰላምና የፍቅር እንዲሆንላችሁ እንመኛለን።

የትንሣኤ በዓል ቤተክርስቲያን ከምታከብራቸው ዐበይት የጌታ በዓላት በታላቅነቱና በክብሩ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘ በዓል ነው፣ የሞት ሽንፈት የክርስቶስ አድኅኖት የሚነገርበት የምሥራች ቀን ነው። በትንሣኤ የክርስቲያኖች ሕይወት ዋስትና ታውጇል፤ ሐሰተኞች የደረደሩት የሐሰት ክስ በሙሉ ተደመሰሰ ሞትም ተሸንፎ የሞት አስፈሪነት ሳይቀር ጠፍቷል፣ ስለዚህ በድጋሚ እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ እንላለን!!

በሰሙነ ሕማማት ስናስበው እንደ ሰነበትን ክርስቶስ ከፉውንና ከፉዎቹን በተቀበለው መከራ መስቀልና በሞቱ ድል ስለነሳቸው ድል ነሺነቱ የተገለጠው በትንሣኤው ነው። ይህንንም መከራውንና ሞቱን በተመለከተ ዳዊት "ብዙ ውሾች ከብበውኛልና የክፉተኞች ጉባኤም ያዘኝ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ። አጥንቶቼ ሁሉ ተቈጠሩ እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም።ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።" መዝ 21፥14-18። ብሎ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦለት አስቀድሞ ተናግሮ ነበር።

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይስም "ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።ተጨነቀ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥እንዲሁ አፉን አልከፈተም።" ኢሳ 53፥ 5-10 ብሎ ስለሁላችን መከራ መቀበሉን ተናግሮ ነበር። መድኃኔዓለም ሞትን በሞቱ ድል ነስቶ ፣ የእኛንም ዕዳ በመስቀል ላይ ሽሮ ፣ በኃይልና በሥልጣን ተነሥቷል።

<u>የትንሣኤው እውነት</u>

በነቢያት የተነገረው ትንቢት እንዴት እንደተፈጸመ አራቱ ወንጌላውያን የሕማማቱን ሁኔታ፣ በሐሰት መከሰሱን ለጠላቶቹ ተሰጥቶ በእነርሱ እጅ መገረፉን፣ መስቀሉን ተሸክሞ እስከ መሰቀያው ቦታ መሔዱን፣ መጨረሻም ከመስቀሉ ላይ ሰውነቱ በሚስማር ተቸንክሮ ከምድር ከፍ ከሰማይ ዝቅ ብሎ መሰቀሉንና ነፍሱን በስቃይ አሳልፎ መስጠቱን በግልጽ ሰብከውልናል ። የክርስቶስ ታሪክ በዚህ ቢያበቃ ክርስትና

እምነት አይሆንም ነበር ቢሆንም ተስፋቢስ እምነት ነበር የሚሆነው።ነገር ግን እግዚአብሔር ያንን ታሪክ በአዲስ ታሪክ ለውጦቷል። አዲሱ ታሪክም የክርስቶስ ትንሣኤ ነው፤ ወንጌሉን የጻፉልን ቅዱሳን ሐዋርያት በትንሣኤው ወቅት የሆነውንና የተደረገውን ታሪክ ያለምንም ጭማሪና ቅናሽ ዘግበዋል፤ በሁሉም ወንጌላውያን በትንሣኤ ጊዜ በሰዎች ዘንድ የነበረውን መደነቅ፣ ድንግርግር፣ ጥርጥር፣ ክህደት እና እውነት መዝግበዋል። በማቴዎስ ወንገል የተዘገበውን ብንመለከተው በቂ ግንዛቤ እናገኛለን። ማቴዎስ በተለያየ አገላለጥ እውነት የሆነውን ነገር ይገልጥልናል። በማቴዎስ ገለጻ መሠረት እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እቅዱን እያከናወነ ሲሆን በሌላው መልኩ ግን የሰው ልጅ የሆነ ሥጋ ለባሽ ሁሉ፣ ፤የክርስቶስ ቀራቢዎችም ጭምር ይህንን ታላቅ ምሥጢር መረዳት አለመቻላቸው ነው። ማቴዎስ የትንሣኤን አስደናቂነት እንዲህ ዘግቦታል።

“መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ።እነሆም፥ የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ። መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ።ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ። መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው። እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና፤ እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ።” ማቴ 28፡1-8።

እነዚህ ለጌታ ቅርብ የሆኑ ሰዎች ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ምንም ዓይነት ግንዛቤ አልነበራቸውም፤ ገና ቀድሞ ገሊላ በነበሩ ጊዜ ስለሞቱ ሲነግራቸው ትንሳኤውንም አብሮ አብሥሯቸው ነበር፣ ግን ዓርብ ማታ ያ ሁሉ ተስፋ አብሮ ከክርስቶስ ጋር ተቀበረ፣ በዚያ ሁኔታ ሳሉ ነው "በዚህ የለም ተነስቷል" የሚለው አዋጅ በመላእከቱ አንደበት የታወጀው።

በዚህ ተአምር በተፈጠረበት ቀን የአይሁድ ሊቃውንት ትንሣኤውን ለማስተባበል ብለው አንድ በጣም ትልቅ ስህተት ሠሩ የስህተታቸው መነሻ በእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እቅድ የተወሰነውንና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተነገረውን የትንሣኤውን ነገር ለማስተባበል መሞከራቸው ነበር። ክርስቶስን ሰቅለው ከገደሉት በኋላ “ ያ አሳች በሕይወቱ ገና ሳለ። ከሦስት ቀን በኋላ እነሣለሁ እንዳለ ትዝ አለን " አሉ፤(ማቴ 27፡63) ስህተታቸው ከዚያ አላበቃም ቀጠሉና ደቀመዛሙርቱ ሰርቀው ሊወስዱ ይችሉ ይሆናል ብለው ከራሳቸው አፍልቅው መጨነቅ ጀመሩ፣ ስለሆነም ጠባቂዎች ይመደቡልን አሉ። ማቴዎስ የሰዎቹን ስሜት እንዲሚከተለው ዘግቦታል።

"እንግዲህ ደቀ መዛሙርቱ መጥተው በሌሊት እንዳይሰርቁት፣ ለሕዝቡም ከሙታን ተነሣ እንዳይሉ፥ የኋለኛይቱ ስሕተት ከፊተኛይቱ ይልቅ የከፋች ትሆናለችና መቃብሩ እስከ ሦስተኛ ቀን ድረስ እንዲጠበቅ እዘዝ አሉት" ጲላጦስን ፤(ማቴ 27፡64)

የአይሁድ ፍርሀት ጠላታችን ነው የሚሉት ሰው በሕይወት ከነበረበት ጊዜ ይልቅ ከሞቱ በኋላ የሚያመጣው ተጽዕኖ ከአቅም በላይ መሆኑን ያስረዳል። በአይሁድ መሪዎች ጥያቄ በመቃብሩ ላይ ጠባቂዎች ተመደቡ፤ ምን ማድረግ እንዳለባቸው መመሪያም ለጠባቂዎቹ ተሰጣቸው። ማቴዎስ ይህንም ሐሳብ በተገቢ መልኩ ያሳያል፤ በጥበቃ አመዳደብ ላይ ብዙ ውዝግብ ነበር፤ ካህናቱ የመንግሥት ጸጥታ አስጠባቂ እንዲመደብ ጠይቀው ነበር፤ ጲላጦስ ግን አይደለም እናንተ ለራሳችሁ የሚሠሩ የራሳችሁ ጠባቂዎች ስለ አሏችሁ የራሳችሁን ጠባቂዎች መድባችሁ አሠሩ አለ፣ ከብዙ ምክክር በኋላ እንዲህ ሆነ “እነርሱም ሄደው ከጠባቆች ጋር ድንጋዩን አትመው መቃብሩን አስጠበቁ።" ማቴ 27፡66

የጥበቃ ቡድኑ ለጥበቃ ከመሳማራቱ በፊት መቃብሩ በጥንቃቄ መገጠም እንዳለበት አምኖ ያንኑ አድርጓል፤ ያ ሁሉ ግን ለዚያ የተአምር ሰዓት መከላከል አላስቻለም ማቴዎስ ይህን በትንሣኤው የተካሔደውን የትንሣኤውን ኃይል በአስደናቂነት እንደሚከተለው ጽፎታል።

"እነሆም፥የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ። መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ።ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ።" ማቴ 28፡2-4

ጠባቂዎቹም ይህን ከሰው ቁጥጥር ውጭ የሆነን ነገር አይቶ ዝም ማለት አልቻሉም የሆነውን ሁሉ ለካህናቱና ለምክር ቤቱ ሽማግሌዎች ተናገሩ። ጠባቂዎቹን የሐሰት ምስክር አድርገው በገንዘብ ሊጠቀሙባቸው ቢፈልጉም የእግዚአብሔር ልጅ ትንሣኤ በሰው ተንኮል የሚጋርድ ባለመሆኑ አልተሳካላቸውም። ክርስቶስን ለማመስገንና የትንሣኤው ምስክር ለመሆን የመጡትን መላእክትም በማለዳ ወደ መቃብሩ የገሰገሱ ሴቶቹ ለዓይን የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው አዩአቸው።

መልአኩም ቅዱሳት አንስትን "እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና፤ እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ "(ማቴ 28፡5-6)አላቸው።

እንዲሁም ቅዱሳት አንስት ሂደው ለሐዋርያት ያዩትንና የሰሙትን እንዲመሰክሩ "ፈጥናችሁም ሂዱና። ከሙታን ተነሣ፥እነሆም፥ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው" አላቸው።(ማቴ 28፡9)

ቅዱሳት አንስት የመጡት ፍቅሩ አስገድዶአቸው እንደ አይሁድ ልማድ የሞተውን መሲህ ሽቱ ለመቀባት ነበር፣ የትንሣኤው ምሥክር ሁነው ተመለሱ። አይሁድ ግን የሐሰት ወሬ በተነሣው ጌታና በትንሣኤው ላይ መናገርን አላቆሙም ነበር ይንንም ሁኔታ ወንጌላዊ እዲህ ሲል ገልጾታል፡-"ከጠባቆቹ አንዳንድ ወደ ከተማ መጥተው የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች አወሩ። ከሽማግሎች ጋርም ተሰብስበው ተማከሩና ለጭፍሮች ብዙ ገንዘብ ሰጥተዋቸው። እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ። ይህም በገዢው ዘንድ የተሰማ እንደ ሆነ፥እኛ እናስረዳዋለን እናንተም ያለ ሥጋት እንድትሆኑ እናደርጋለን አሉአቸው እነርሱም ገንዘቡን ተቀብለው እንደ አስተማሩአቸው አደረጉ። ይህም ነገር በአይሁድ ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ ሲወራ ይኖራል" (ማቴ 28፡11-15)

አሁንም ማቴዎስ የክርስቶስን ደቀመዛሙርትና የመላእክትን ነገር ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚዎችን ሥራ ጭምር ይገጽልናል፤ ጠባቂዎች ሁኔታውን የተመለከቱ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ኃይል ተይዘው የዓይን ምስክር የሆኑበትን እውነት እንዲጠብቁ ለመደቧቸው አለቆቻቸው ሪፖርት አቀረቡ፣ ይህ ሁኔታ ሲካሔድ እንቅልፍ በሚያስወስድ ሁኔታ ላይ የተከናወነ አልነበረም፤ ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ በሆነ ሁኔታ ነበር ትንሣኤው የተከናወነው። ሆኖም አለቆቹ ይህን እውነት በኃይልና በገንዘብ ለመቆጣጠር ወስነው ትንሣኤውን ካዱት፤ ይህም የክህደት ጉዳይ እስከ ዛሬ ድረስ ይወራል አለ ማቴዎስ፣ነገርግን የተነሣው ጌታ የእውነት አምላክ በመሆኑና ትንሣኤውም እውነት በመሆኑ የሐሰት አባት ዲያብሎስንም ሆነ የግብር ልጆቹን የሀሰት ወሬ ሽሮ በእውነት የትንሣኤውን ብርሃን በሰዎች ልቡና ውስጥ በማብራት በሞቱ ያዳናቸውን ሁሉ በትንሣኤው አጸደቃቸው።

## የተወደዳችሁ ኦርቶዶክሳውያን

በዚህ በትንሣኤው ታሪክ ላይ ተመስርተን ዘመናችን ብንዋጀው ተመሣሳይ ታሪክ እንመለከታለን። አሁን በአለንበት ዘመን እንደ ጥንቱ ሁሉ ብዙ መዋዕለ ንዋይ እውነትን ለመቅበር ይፈሳል፤ አሁን ይህን የነጻነት

በአል እያከበርን ብዙ ንጹሐን ወገኖቻችን በእስር ቤት ታጉረዋል፤ ብዙ ሕጻናት የሚበሉት አጥተው በረሐብ አለንጋ እየተገረፉ ነው፤ ብዙ አባወራዎች ለመለመን አፍረው የትንሣኤውን በአል ማክበር አቅቷቸው በስቃይ ላይ ናቸው፤ በሀገራቸው በነጻነት የመኖር መብታቸውን ያጡ በደቡቡ የነበሩት ወገኖቻችን የሚያርሱትን መሬታቸውን፣ ያፈሩትን ንብረታቸውን ተቀምተው በሀገራቸው ላይ ተሰደው ትንሣኤን በሐዘን እያሳለፉ ነው።

በአፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ በተለይም በሀገራችን በኢትዮጵያ ይህ ችግር የተለመደ ሆኗል፣ የዛሬ ሁለት ሽህ አመት በዛሬው ቀን የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎችና የሮማ ተባባሪዎች ክርስቶስን በሐሰት ለፍርድ አቅርበው በሐሰትና በአመጽ ሰቅለው ክርስቶስን ገደሉት፤ እግዚአብሔር ግን ይህን በአመጸኞች ትብበር የተደረገን የሰው አድማ በትንሣኤ ደመሰሰው ፣ ትንሣኤ ያበሠረው የክርስቶስን መነሣት ብቻ አይደለም የእውነትንም መነሣት ጭምር ነበር ያበሰረው፤ ለአምባገነኖች አይምሰላቸው እንጅ እውነት ተቀብራ አትቀርም ፤እውነት ነጻ ታወጣለች ሲባል እውነት ራሷ ነጻነት ስለሆነች ነው፣ ራሷ ነጻነት ባትሆን ኑሮ ሌላውን ነጻ አታወጣም ነበር።

በወንጌሉ እንደ ተገለጠልን የክርስቶስ ተከታዮችም መጀመርያ ክርስቶስ ይነሣል ብለው ሙሉ በሙሉ አላመኑም ነበር፤ ግን ጌታችን እንደተናገረ ተነሣ፤ ዛሬም በመከራና በእስር ላይ ያሉ ሁሉ መከራው የማያልፍ አይምሰላቸውም ይሆናል ነገር ግን የትንሣኤ ጌታ በሕይወት እያሉ ነጻነታቸውን አጥተው፣ ከሕዝባቸው ከቤተ ሰባቸው ተለይተው፣ በእስር ቤት በስደት የሚገኙትን ወገኞቻችንን ሁሉ ፣ ከተጣሉበት እስር ቤት ከደረሰባቸው ፈተና ከከፉ የአገዛዝ ቀንበር ነጻ ሊያወጣቸው የታመነ ነው። ይህን እውነት ከታሪክ እንማራለን የትንሣኤው ታሪክ በተመዘገበት ዘመን የዛሬ ሁለት ሽኽ ዓመት ሮማውያን ዓለምን ያስጨነቀ ስልጣን ነበራቸው ያ አሁን የለም በምትኩ ያን ጊዜ ያልነበሩ አገሮች አሁን የዓለም ቁንጮ ናቸው ይህም ያልፋል።

በኛ ዘመን ደግሞ ሞቱንና ትንሣኤውን እየመሰከሩ ለሀገራችን እየጸለዩ የሚኖሩ መናንያን ትንሣኤውን በሐዘን እንዲያሳልፉት በመደረጉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጣም አዝናለች፤ በገዳማቶቻችን ላይ እየተደረገ ያለው የጥፋት ዘመቻ የሚቆምበት ቀን እሩቅ አይሆንም ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ግራኝም አልፏል እሱን ያስታጠቀው የኦትማን አገዛዝም የለም ይህ አውነት ነው። ክርስቲያን ወገኖቻችን ሆይ ተስፋ አትቁረጡ ከዚህ ይልቅ በዚህ በትንሣኤው ተስፋ ተባበሩ፤ አንዱ ላንዱ ይቁም ትንሣኤ እንድናከብረው የሚያደርገን ክርስቶስ ስለተነሣ ብቻ አይደለም እኛም ስለ ምንነሣ ነው እንጅ፣ ይህ የትንሣኤ ተስፋ አንዳንፈራ ለእውነት እንድንቆም ያደርገናል። ክርስትናም ዋናው ተስፋው የክርስቶስ ትንሣኤ ነው፤ ምክንያት የክርስቶስ ትንሣኤ የነጻነትና የድል መሠረት ስለሆነ ነው።

እንግዲያውስ ሐዋርያው ጳውሎስ "ክርስቶስ ከሙታን እንደ ተነሣ የሚሰበክ ከሆነ ግን ከእናንተ አንዳንዶቹ። ትንሣኤ ሙታን የለም እንዴት ይላሉ? ትንሣኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣማ፤ ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት፤ደግሞም፦ ክርስቶስን አስነሥቶታል ብለን በእግዚአብሔር ላይ ስለ መሰከርን ሐሰተኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል፤ ሙታን ግን የማይነሡ ከሆነ እርሱን አላስነሣውም።ሙታን የማይነሡ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሣማ፤ ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ። እንግዲያስ በክርስቶስ ያንቀላፉት ደግሞ ጠፍተዋላ።በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ፥ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን።" ፩ቆሮ15፡12-19

የክርስቲያኖች እምነትና ትምክህት የክርስቶስ ትንሣኤ ነው የክርስቶስ ትንሣኤ ደግሞ ለእኛ ትንሣኤ ማረጋገጫ ሁኗል ለዚህ ነው ገዳማዉያኑ ሁሉ ዓለምን ንቀው ወደ በርሃ የገቡት፤ አምባገነኖች መኖሪያ ቢያሳጧቸውም እነርሱ በትንሣኤው ተስፋ ይኖራሉ፤ በታሪክ ውስጥ የዓለም መሪዎች ክርስትናን

ለማጥፋት ያላደረጉት ጥረት የለም፤ አሁን የእኛዎቹ እንደሚያደርጉት ሁሉ ሌሎቹ በአለፈው ሁሉት ሽኽ ዓመት አድርገውታል ብዙ ክርስቲያኖችን ገድለዋል፤ በእሳት አቃጥለዋል ፣ስማቸውን አጥፍተዋል፣ ዛሬም መሰሎቻቸው ያንኑ ያደርጋሉ ፣ትልቁ የምሥራች ግን እነዚያ አምባ ገነኖች ዛሬ ሁሉም የሉም፣ ስማቸውም የለም፣ ቅዱሳኑ ግን አሁንም በምድር ስማቸው ሕያው ነው አንደገናም ለዘለዓለም ሕይወት ዋስትና በሆነው የትንሣኤ ተስፋ ተጠብቀው ይኖራሉ። ይህ የትንሣኤው ተስፋና ኃይል ነው ከአውሬ ጋር እንዲታገሉ ከሰይፍ ጋር ፊት ለፊት እንዲጋፈጡ በስደት እንዲንከራተቱ ያደረጋቸው፤ ተሰዳጆቹ በትንሣኤው ተስፋ ሲኖሩ አሳዳጆቹ ተስፋ ቢስ ሁነው ይሞታሉ፤ አሁን የመንፈስ ትንሣኤ ስለሌላቸው መጨረሻቸውም ያ ዘለዓለማዊ ሞት ነው።

በስተመጨረሻም በክርስቶስ ትንሣኤ ሁላችንም ለዘለዓለም ሕይዎት ስለተዘጋጀን እንደ ክርስቶስ፣ የሚሞተው አካላችን የሚሞተውን ለብሶ የሚነሳበትን ዕለተ ትንሣኤ በተስፋ እንጠብቃለን። ቅዱስ ጳውሎስ "ዳሩ ግን ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሲለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ፥ በዚያን ጊዜ። ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል። ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ?"1ቆሮ 15፡54 ብሎ እንደተናገረ።

ቤተክስቲያንም በዚህ በትንሣኤው ሰሞን በምትለዋወጠው የሰላምታ ቃል መልክታችንን እንገታዋለን።
" ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን፣ በዐቢይ ኃይል ወስልጣን፣አሰሮ ለሰይጣን፣ አግአዞ ለአዳም ፣ ሰላም እምይእዜሰ ኮነ ፍሥሐ ወሰላም።
ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ተነሣ፣ ሰይጣንን አሰረው፣ አዳምን ነጻ አወጣ ከዛሬ ጀምሮ ሰላምና ደስታ ሆነ።"

ምስጋና ውዳሴ ሞትን ድል ለነሣው አምላካችን ይሁን፣ ከበረከተ ትንሣኤው ይክፈለን።

እግዚአብሔር አምላክ ለሀገራችን ሰላምን ለቤተክርስቲያናችን አንድነትን ይስጥልን አሜን።

አባ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ

የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ